በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፫

## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:-** kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ታህሳስ ፲፯ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም.**

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፫

- ኑኃሚን ሩትን ወደ ቦዔዝ አውድማ ወርዳ በሚተኛበት ሥፍራ እንድትገናኘው መከረቻት፡፡ ሩትም ወደ ቦዔዝ ሄዳ መሐሉን ከሞተ ወዲህ ብቻዬን ነኝና ዋርሳ ሁነኝ ብላ ጠየቀችው፡፡
- የኑኃሚን የልብ መሻትዋ (ሕግ) ሩት ከሙሽራው (ክርስቶስ) ጋር እንድትዋሐድና እንደ ሕጉ የሞተው ልጅዋ ዘር ተቆርጦ እንዳይቀር ይቀጥል ዘንድ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ቦዔዝን በአውድማው፣ በሚተኛበት፣ ምስጢር በሚፈጸምበት በማታ የግል እንድትገናኘው መከረቻት፤ በዚያ ሩት የቦዔዝን ድምጽ መስማት፣ ቃል ኪዳኑንም መቀበል፣ ከርሱም ጋር ደስ ልትሰኝ በእቅፉም ልትሆን ትችላለችና
- ‹‹እንግዲህ ታጠቢ፥ ተቀቢ፥ ልብስሽን ተላበሺ፥ ወደ አውድማውም ውረጂ ነገር ግን መብሉንና መጠጡን እስኪጨርስ ድረስ ለሰውዮው አትታዩው። በተኛም ጊዜ የሚተኛበትን ስፍራ ተመልከቺ፥ ገብተሽም እግሩን ግለጪ፥ ተጋደሚም የምታደርጊውንም እርሱ ይነግርሻል።›› ***ሩት 3:3-4::***
- ኑኃሚን ለሩት የመከረቻት ምክር ከቦዔዝ ጋር አንድ እንድትሆን ምክንያት ሆኗል፡፡ የሆነውም፡-
  - በመታጠብ፡- በጥምቀት - ያልተጠመቀ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስምና
  - በመቀባት፡- በሜሮን - የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ በሕይወትዋ ትታደስ ዘንድ
  - በመልበስ፡- ልብሳችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና ‹‹ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና።›› እንዳለ ***ገላ 3:27::***
  - ወደ አውድማው በመውረድ፡- ፍሬን ከገለባው ከሚለይ መስፍን እንድትገናኝ
  - መብሉንና መጠጡን እስኪጨርስ፡- ብቻውን (በፍቅር የሚኖር ምስጢራዊ ንግግር) እንዲሆን
  - እግሩን በመግለጥ፡- የዓለምን ሐሳብ በመተው ወደ መለኮት ፍቅር በመቅረብ ስጦታውን ፈልጎ በመሰብሰብ እንድትመላለስ፡፡ በወዲያኛው ዓለምም ከአምላካችን ጋር ፊት ለፊት እንገናኛለን፡፡
  - በመጋደም፡- በትንሣኤው ኃይል ደስ ለመሰኘት ከርሱ ጋር መሞትንና መቀበርን በመቀበል ነበር

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፫

***የሩትና የቦዔዝ መገናኘት***

- ‹‹ ወደ አውድማውም ወረደች፥ አማትዋም ያዘዘቻትን ሁሉ አደረገች። ቦዔዝም ከበላና ከጠጣ ሰውነቱንም ደስ ካሰኘ በኋላ፥ በእህሉ ክምር አጠገብ ሊተኛ ሄደ ሩትም በቀስታ መጣች፥ እግሩንም ገልጣ ተኛች። መንፈቀ ሌሊትም በሆነ ጊዜ ሰውዮው ደነገጠ፥ ዘወርም አለ እነሆም፥ አንዲት ሴት በእግርጌው ተኝታ ነበረች። እርሱም፦ ማን ነሽ? አለ። እርስዋም፦ እኔ ባሪያህ ሩት ነኝ ዋርሳዬ ነህና ልብስህን በባሪያህ ላይ ዘርጋ አለችው። ቦዔዝም አላት። ልጄ ሆይ፥ በእግዚአብሔር የተባረክሽ ሁኚ ባለጠጋም ድሀም ብለሽ ጕበዛዝትን አልተከተልሽምና ከፊተኛው ይልቅ በመጨረሻው ጊዜ ቸርነት አድርገሻል። አሁንም፥ ልጄ ሆይ፥ አትፍሪ በአገሬ ያሉ ሕዝብ ሁሉ ምግባረ መልካም ሴት እንደ ሆንሽ ያውቃሉና ያልሽውን ነገር ሁሉ አደርግልሻለሁ። የቅርብ ዘመድ መሆኔ እውነት ነው ነገር ግን ከእኔ የቀረበ ዘመድ አለ። ዛሬ ሌሊት እደሪ ነገም እርሱ ዋርሳ መሆን ቢወድድ መልካም ነው፥ ዋርሳ ይሁን ዋርሳ ሊሆን ባይወድድ ግን፥ ሕያው እግዚአብሔርን እኔ ዋርሳ እሆንሻለሁ እስኪነጋ ድረስ ተኚ።›› ሩት 3፡6-13፡፡
- **የርሱ ጥበቃ የሚያስፈልጋት ዘመዱ መሆንዋን ለመግለጥ እግሩን ገልጣ ተኛች፡፡ ቦዔዝም ሩትን ስለ አስተዋይነትዋና ለቀደመው ባልዋ ለመሐሎን ስላሳየችው ታማኝነትዋ አመሰገናት፤ ባለጠጋና ድኃ ብላ ወደ ጎበዛዝት ሳትሔድ ወደ መሐሎን የቅርብ ዘመድ በመምጣት የቅርብ ዘመድ ኃላፊነቱን እንዲወጣ ዋርሳም እንዲሆናት ጠይቃዋለችና በቦዔዝ ተመሰገነች፡፡**

***የሩት ወደ አማትዋ ኑኃሚን መመለስ***

- ‹‹ እስኪነጋም በእግርጌው ተኛች ቦዔዝም። ሴት ወደ አውድማው እንደ መጣች ማንም እንዳያውቅ ብሎ ነበርና ገና ሰውና ሰው ሳይተያይ ተነሣች። እርሱም፦ የለበስሽውን ኩታ አምጥተሽ ያዢው አላት በያዘችም ጊዜ ስድስት መስፈሪያ ገብስ ሰፈረላት አሸከማትም። እርሱም ወደ ከተማይቱ ሄደ። ወደ አማትዋም መጣች፥ አማትዋም። ልጄ ሆይ እንዴት ነሽ? አለቻት እርስዋም ሰውዮው ያደረገላትን ሁሉ ነገረቻት። ወደ አማትሽ ባዶ እጅሽን አትሂጂ ብሎ ይህን ስድስት መስፈሪያ ገብስ ሰጠኝ አለቻት። እርስዋም፦ ልጄ ሆይ፥ ሰውዮው ይህን ነገር ዛሬ እስኪጨርስ ድረስ አያርፍምና ፍጻሜው እስኪታወቅ ድረስ ዝም በዪ አለች። ›› ሩት 3፡14-18፡፡
- **ሩትም በቀን ከምትሰበስበውም እጥፍ መስፈሪያ ገብስ ይዛ ተመለሰች፤ ቦዔዝ ሰጥቷታልና፡፡**

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፫

*__የሩት ወደ አማትዋ ኑኃሚን መመለስ__*

- ሰው በጸሎት በመትጋት፣ በደጅ ጥናትም የሚያገኘው በመሻት ከሚያገኘው በእጥፍ ይበልጣል፡፡ በቦታው ሳይኖር በስጦታው ሳይተጋበት፤ በደጅ ጥናት ከሚገኘው ሀብት ሊያገኝ የሚችል የለም፡፡
- ኑኃሚን ሩት ተመልሳ ስትመጣ ‹‹ልጆ ሆይ አንቺ ነሽን እንዴት ነሽ?›› ብላታለችና አላወቀቻትም ነበር፡፡ ይህም ኑኃሚን በሩት ደስ መሰኘትዋንና ሁላችንም ከክርስቶስ ጋር በምናደርገው የዘወትር ግኑኝነት የምናገኘውን ደስታና የምንቀዳጀውን ድል የሚያመለክተን ነው፡፡

*__ሩትና ሰማያዊ ሠርግ__*

- እንደ ሕጉ ሊወስዳት ከሚገባው የቅርብ ዘመድ ነጻ ስትሆን ቦዔዝ ሩትን ሙሽራይቱ አድርጎ ሊወስዳት በከተማይቱ መግቢያ ተቀመጠ፡፡ የቅርብ ዘመድ ሊቤዥ አልፈቀደምና የሞቱትን ዘር ከፍ ያደርግና አቤሜሌክንና ልጆቹንም ይቤዥ ዘንድ ቦዔዝ ወደደ፡፡
- በከተማይቱም መግቢያ የሽማግሌዎች ጉባኤ ተደረገ፤ ሩትን (የሰዎችን ነፍሳት) ከዋርሳዋ (ሰዎችን ከሚገዛው ከዲያቢሎስ ተገኚዘነት) ነጻ ወደ መውጣት ያመሩት  የተመረጡትም አሥሩ ሽማግሌዎች የአሥሩ ትእዛዛት ምሳሌ ሲሆኑ እነርሱም ቦዔዝ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ሙሽራይቱን ዘርዋን ከሙታን ከፍ ያደርገ ከቁራኝነትም ነጻ ያወጣው ነው፡፡
- የቅርብ ዘመድ ዋርሳ ሊሆን (ሩትንም ሊታደጋት) አልፈቀደም ነገር ግን ይቤዥ ዘንድ የሚቻለው ቦዔዝ(ኢየሱስ ክርስቶስ) ይቤዥ ዘንድ ራሱን አቀረበ፡፡ ይህም የቅርብ ዘመዱ ሊወርስ የሚገባውን የአቤሜሌክንና የልጆቹን ርስት ሁሉ ለቦዔዝ አሳልፎ መስጠቱን ያመለክተናል፡፡

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፫

***የሩት ወደ አማትዋ ኑኃሚን መመለስ***

- ቦዔዝ የፈለገው የአቤሜሌክን ርስት ወይም መሬት ሳይሆን ሩትን ነበር፤ ይህም ልጆችን ወልዳ የምዋቹ ስም እንዳይጠፋ ነው። ***ሩት 4:10።***
- በከተማይቱም በር የነበሩ ሽማግሌዎችም ቦዔዝ ራሱን የሰጠበትን ሕይወት እንደሚከተለው መረቁ፦
    - እግዚአብሔር አሥራ ሁለቱን ነገድ የወለዱትን የያዕቆብን ሚስቶች እንደባረከ ሚስቱን ሩትን ባረኩ
    - ስምህም በቤተልሔም ይጠራ፣ በኤፍራታም ባለጠጋ ሁን አሉት፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ከመሆን የበለጠ ስም አለን?
    - ቤትህም ትዕማር ለይሁዳ እንደወለደችው እንደ ፋሬስ ከሩት በሚሰጥህ ዘር የተባረከ ይሁን አሉት። ***ዘፍጥ 38:29-30***፤
- ሩትም ኢዮቤድን ወለደች፤ እርሱም በእግዚአብሔር የነበራት እምነትዋ ፍሬና ከሞት በኋላ ሕይወትን የሚሰጠው የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው።
- ኢዮቤድ (ባሪያ) ‹‹ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ ›› ***ፊል 2:7።*** እንዳለ የባሪያን መልክ ይዞ የተመላለሰው፣ የኑኃሚንን እርጅናዋን በመውሰድ ሰውነትዋን ያደሰው የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። ልጅዋም ለሩት ሰባት ወንዶች ልጆች ከማግኘት የሚበልጥ ነበር። ሰባቱ ልጆችም የእግዚአብሔር ስጦታ ምሳሌ ሲሆኑ እውነተኛው ኢዮቤድ ታላቅ መሆኑ ንጉሠ ነገሥት ፈጣሪ ፍጡራን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ያመለክተናል።

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፫

***የሩት ወደ አማትዋ ኑኃሚን መመለስ***

- ኑኃሚን ኢዮቤድን ማቀፍዋ፣ ሞግዚት መሆንዋና በርሱም ደስ መሰኘትዋ ስለ መሲሑ የተነገረው የነቢያት ትንቢትና ሕግ መፈጸሙንና የሚያመለክተን ምሳሌ ነው፡፡
- መጽሐፉ ከአያቱ ከሩት ፍሬ ሆኖ ዳዊት የሚወለድ መሆኑን በማወጅ ይጠናቀቃል፡፡ ‹‹ቦዔዝም ኢዮቤድን ወለደ፥ ኢዮቤድም እሴይን ወለደ፥ እሴይም ዳዊትን ወለደ።›› ***ሩት 4:22፡፡***
- የንጉሡ የመድኃኔዓለም የትውልድ ቁጥሩ በአይሁድ ጀምሮ ከሰማያዊው (መንፈሳዊው) ንጉሥ ዘንድ በንጉሡ በዳዊት በኩል ያደርሰናል፡፡
- መጽሐፉ መጽሐፈ ሩትም አቤሜሌክ ቤተሰቡን ይዞ ከረሐቡ ሸሽቶ ወደ ሞዓብ በመሸሹ ይጀምርና ዓለሙ ሁሉ ፍጹም እርካታ ባገኘበትና ዓለሙ ሁሉ በሚሻው በዳዊት ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደመደማል፡፡

***ማጠቃለያ***

- ሩት በሞዓብ፣ በቦዔዝ እርሻ፣ በቦዔዝ አውድማ በተግባር ያሳየችውን እምነትዋን አስመልክቶ ተወያይታችሁ እንደርስዋ በዝቅታው፣ በማዕከላዊነትም ሆነ በከፍታው እምነታችንን በተግባር ለማሳየት ምሳሌ አድርገን እንጠቀምባት፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org